# በረከተ ወንጌል

በዚህ ዓምድ ሥር የጌታችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የሚያስተምረንን ሕይወት በተከታታይ እናቀርባለን።

## ጸሎትህ ተሰምቶልሃል

ከዲ. ተክለወልድ

ሰው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ለእግዚአብሔር ስለተፈጠረ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ይፈልጋል። መገናኛውም ጸሎት ስለሆነ ይጸልያል። ቀደምት አበው (የቀደሙ አባቶች) ጸሎት በሰቂለ ኅሊና በአንቃዕድዎ ልቡና በሰፊሃ እድ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር እንደሆነ ነግረውናል። ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ያለን የመገናኛ ምልክትና ማጸኛ ነው። ጸሎት ጎብረትን፣ ምስጋናን፣ ስግደትን፣ ንስሐን፣ ልመናን፣ ምልጃን ያጠቃልላል። ሰዎች በልዩ ልዩ አቋቋም ቦታና ጊዜ ሊጸልዩ ይችላሉ። ዋናው ነገር ግን የልብ መሰበር ነው። ነቢዩ ዳዊት እንዳለ፣ «የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም» መዝ.50፥17። ቃሉም ትህትናን ገንዘብ ማድረግ እንዲገባ ያስተምረናል።

በሕይወቱ ውስጥ ጉድለት ያለበት ሰው ሁሉ የጨለመው እንዲበራለት፣ የጠመመው እንዲቃናለት፣ የጠወለገው እንዲለመልምለት፣ የተዘጋው እንዲከፈትለት፣ የተዘራው እንዲበቅልለት፣ የተተከለው እንዲጸድቅለት፣ የተወለደው እንዲያድግለት፣ የተበተነው እንዲሰበሰብለት፣ የተሰበሰበውም እንዲባረክለት ልመናውን በጸሎት ለእግዚአብሔር ያቀርባል። እግዚአብሔርም የልጆቹን ጸሎት በደስታ ይሰማልና ጸሎት ብዙ ኃይል አለው። 1ጴጥ.3፥12፤ያዕ.5፥17። ጸሎቱ የተሰማለት ሰው ፈጥኖ ከሐዘኑ ይጽናናል። ከጭንቀቱ ይረጋጋል። ከችግሩ ባሕር ይወጣል፣ ከድካሙ ይበረታል።

በትእዛዙና ሕግጋቱ ሲመዘን ያለነቀፋ የሄደና በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ የነበረ ካህን ዘካርያስ በአዲስ ኪዳን ዋዜማ እንደ ካህናት ሥርዓት ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ጽንሐውን ይዞ በሚያጥንበት ጊዜ ከዕጣኑ መሠዊያ በስተቀኝ መልአኩን በማየቱ ደነገጠ፤ ፍርሃትም ወደቀበት። ሉቃ.1፥11–13። ተፈጥሮአቸው ከማይጠፉ እሳትና ነፋስ የሆኑ ቅዱሳን መላእክት ኃይላቸው ታላቅ ስለሆነ የሚያስፈራና የሚያስደነግጥ ግርማ አላቸው። መዝ.12፥20:13፥4። እንኳን ሰው ምድር በፊታቸው ትንቀጠቀጣለች። እጅግም የሚያስ ፈሩ ናቸው። መልካቸው እንደ መብረቅ ልብሳቸውም እንደ በረዶ ነጭ ነውና። ማቴ.28፥2።

በዚህ ሁኔታ ለዘካርያስ የተገለጠው መልአክ፣ «ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ» ብሎ ካረጋጋው በኋላ ሚስቱ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ እንደምት ወልድ ስሙም ዮሐንስ እንደሚባል ለዘካርያስም ተድላና ደስታ እንደ ሚሆንለት በመወለዱም ብዙዎቹ ደስ እንደሚላቸው በጌታ ፊት ታላቅ እንደሚሆን የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ እንደማይጠጣ በእናቱም ማኅፀን ሳለ በመንፈስ ቅዱስ እንደ ሚ.ቃኝ፣ ከእስራኤልም ልጆች ብዙዎቹን ወደ አምላካቸው እንደሚ መልስ የተዘጋጁትን ሕዝብ ለጌታ እንዲያሰናዳ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ በኤልያስ መንፈስና ኃይል በፊቱ እንደሚሄድ ለዘካርያስ በዝርዝር ነገረው። ይህ ሁሉ ሲሆን በዕጣኑ መሥዋዕት ጊዜ በውጭ ይጸልዩ የነበሩት ሕዝብ በዘካርያስ መዘግየት ከመደነቅ በቀር ምንም አላወቁም። ዘካርያስ፣ «እኔ ሽማግሌ ነኝ ሚስቴም በዕድሜዋ አርጅታለችና ይህን በምን ዐውቃለሁ» በማለቱ መልአኩ መለሶ፣ «እኔ በእግዚአብ ሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ እንድናገርህም ይህችንም የምሥራች እንድሰብክልህ ተልኬ ነበር። እነሆም በጊዜው የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንህ ዲዳ ትሆናለህ መናገርም አትችልም» ስለአለው ወዲያው ዲዳ ሆነ። ከመቅደስም በወጣ ጊዜ ለመና ገር ባለመቻሉ ሕዝቡ ራእይ እንዳየ አስተዋሉ። እግዚአብሔር ለወዳጆቹ በራእይ ይገለጣልና በሕልምም ያነጋግራቸዋልና። ዘኍል.12፥6። ሉቃ.1፥8–23።

በብሉይ ኪዳን ታሪክ ነቢዩ ዳንኤል በኡባል ወንዝ መካከል ቅዱስ ገብርኤልን ጡግሮስ በተባለው

በታላቁ ወንዝ አጠገብ በፍታ የለበሰውንም ጥሩም የኦፊዝን ወርቅ በወገቡ የታጠቀውን አካሉም እንደ በረሌ፥ ፊቱም እንደ መብረቅ እግሮቹም እንደ ጋለ ናስ የሚመስለውን የቃሉም ድምፅ እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ የነበረውን መልአክ ባየ ጊዜ እንደ ፈራ እንደተንቀጠቀጠ፤ እንደ ደነገጠ እና እንደሰገደ የዘካርያ ስም ፍርሃትና ድንጋጤ ከዚሁ እንግር ነበር። በዚህም አባቶቹን ነቢያትን መስሎ ተገኝቷል። ዳን.8፥16፡ 10፥8። አባቱን የማይመስል ልጅ ግን ዲቃላ ነው። ዘዳግ.23፥2። ዕብ.12፥8። ዲቃላ ያይደለ የሕግ ልጅ ዘካርያስ መላእክትን ማክበር እንደ አባቶቹ ገንዘብ አደረገ።

ነቢዩ ዳንኤል በማታ መሥዋዕት ጊዜ ስለራሱና ስለሕዝቡ ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ሲጸልይና ሲና ዘዝ ጸሎቱ ስለተሰማለት መሥዋዕቱ ስለሠመረለት ቅዱስ ገብርኤል እየበረረ መጥቶ ዳሰሰው፥ አስተማረው፥ ተናገረው። በአዲስ ኪዳን መግቢያ በር ላይ የነበረውም ጻድቅ ካህን ዘካርያስ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ስለራሱም ሆነ ስለሕዝቡ ሲጸልይና መሥዋዕተ ዕጣን ሲያሳርግ መልአኩ ተገልጦ አነጋገረው። ዳን.9፥20። ሉቃ.1፥13። ዕጣን ጸሎትን የሚያሠምር የመዓዛ መሥዋዕት ነውና። ራእ.8፥3–4።

ሥጋንና እንጀራን ከመብላት የወይን ጠጅን ከመጠጣትና ዘይትም ከመቀባት ተከልክሎ ሰውነቱን በጾምና በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት አዋርዶ ለነበረው ነቢይ ለዳንኤል መልአክ እግዚአብሔር ተገልጦ የተወደድህ ሰው ዳንኤል ሆይ አትፍራ ልብህ ያስተውል ዘንድ ሰውነትህም በአምላክህ ፊት ይዋረድ ዘንድ ካደረግህበት ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ቃልህ ተሰምቶአል። እኔም ስለቃልህ መጥቻለሁ በማለት ፍርሃትን አርቆ እንዳበሰረው ለዘካርያስም «ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ» ብሎ ጸሎቱ ቅድመ እግዚአብሔር መድረሱን ነገረው። ዳን.10፥12። ሉቃ.1፥13። በዘመኑ ሐዋርያት ለቆርኔሌዎስ «ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ እንዲሆን ዐረገ» ተብሎ በመልአክ ቃል እንደተነገረው ማለት ነው። የሐዋ.10፥4።

ባለጠግነቱ ጥበቡና ዕውቀቱ ጥልቅ ፍርዱ የማይመረመር ለመንገዱም ፍለጋ የሌለው እግዚአብሔር ለማራ ካረጀች ካፈጀች በኋላ ይስሐቅን፥ ለመካኒቱ የማኑሄ ሚስት በብሥራተ መልአክ ኃያሉ ሶምሶንን፥ በልጅ ዕጦት ብስጭት ከስታ ጠቁራ ከመብል ከመጠጥም ተከልክላ ለነበረች ለሕልቃና ሚስት ለሐና ነቢዩ ሳሙኤልን እንደሰጠ ለዘካርያስና ለኤልሳቤጥም የሆድ ፍሬ ዋጋ ሊከፍላቸው የልጅ ስጦታ ሊሰጣቸው ፈቀደ። ዘፍጥ.18፥14። መሳ.13፥2። 1ሳሙ.1፥19። ሮሜ 11፥33። ነቢዩ ዳዊት እንዳለው «እነሆ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው የማሕፀንም ፍሬ ዋጋ ናቸው» መዝ.126፥3። ዘፍጥ.30፥2።

ዘካርያስ ሕገ እግዚአብሔርን አክብሮ የመቅደሱን አገልግሎት አጽንቶ እምነትን ከምግባር አዋሕዶ በመገኘቱ በፍሬ ምግባር ላይ ፍሬ ማኅፀን እንደሚጨመርለት የሚገልጠውን ቃል ሰማ፤ ይህም በጸጋ ላይ ጸጋ በበረከት ላይ በረከት መሆን ነው። በብሉይ ኪዳን ልጅ አለመውለድ ልዩ ትርጉም ነበረውና የዘካርያስም ኀዘኑ ይኸው ነበረ። ይሁንእንጂ መልአኩ፥ «ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች። ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ደስታና ተድላም ይሆን ልሃል» አለው። በተለይም የእግዚአብሔር ምሳሌና ክብር የሚሆን ወንድ ልጅን መውለድ ታላቅ ደስታ ነበረ። የያዕቆብ ሚስት ልያ ለባልዋ ደጋግማ ወንዶች ልጆች በመውለድዋ «ደስታ ሆነልኝ ሴቶች ያመሰግኑኛልና» ብላለች። ዘፍጥ.30፥13። 1ቆሮ.11፥3።

የይስሐቅ መወለድ የአብርሃምና የሦራ፥ የሶምሶን መወለድ የማኑሄና የሚስቱ፥ የሳሙኤል መወለድ የሕልቃናና የሐና ደስታ ነበረ። የዮሐንስ ግን ልዩ ነው። ምክንያቱም ደስታው በወላጆቹ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ለብዙዎች ሰዎች ጭምር እንደሚሆን መነገሩ ነው። ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬያት አንዱ ደስታ በመሆኑ ዮሐንስን ደስታ ነው ለማለት ይቻላል። ገላ.5፥22። ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ፍሬ ደስታ ዮሐንስን እንዲያፈሩ እግዚአብሔር የተከላቸው ዛፎች ናቸው «መልካም ዛፍ መልካም ፍሬ ያፈራልና» ማቴ.6፥17። መልካም ዛፍ የደጋግሰዎች ቅጠል የሃይማኖታቸው ፍሬ የምግባራቸው ምሳሌ ነው።

የዘካርያስና የብዙዎች ሰዎች ተድላና ደስታ የሚሆን ዮሐንስ ወደፊት ጌታን በማጥመቅ መጥመቁ መለኮት በመስኘት ታላቅነቱ የሚገለጥ ነውና «በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና» ተባለ። ይህ ታላቅነት የሚገኘው ራስን በሰውና በፈጣሪ ፊት በትህትና በማሳነስ ነው። ማቴ.20፥26፡ 23፥12። ሉቃ.22፥26። ያዕ.1፥9፡ 4፥10። ምሳ.29፡23። ከማኅፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ በመሆኑ የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ እንደማይጠጣ ተነገረለት። ይህ ምልክት በእሥራኤል ዘንድ ልማድ ነበረ። «ሰው ወይም ሴት ለእግዚአብሔር ራሱን የተለየ ያደርግ ዘንድ የናዝራዊነት ስዕለት ቢሳል ከወይን ጠጅና ከሚያሰክር መጠጥ ራሱን የተለየ ያድርግ» ይላል። ዘኁል.6፥2። ሶምሶን ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ እንደሚሆን ተነግሮለት ነበር። መሳ.13፥7። ዋናው ነገር

ለአገልግሎት የተመረጠና የተለየ ሰው መሞላት ያለበት በእግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በወይን ጠጅ አይደለም። ሉቃ.21፥34። ሮሜ 13፥13። ኤፌ.5፥18።

ነቢዩ ዳዊትን በእናቱ ማሓፀን ሳለ ሰውሮ ግሩምና ድንቅ ሆኖ እንዲፈጠር ያደረገ፤ ነቢዩ ኤርምያስንም ገና በማሓፀን ሳይፈጥረው ያወቀው በማኅፀንም ሳለ የቀደሰው አምላክ ዮሐንስም በእናቱ ማኅፀን እያለ በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላ እንዲቀደስም ፈቃዱ ሆነ። መዝ.138፥13። ኤር.1፥5። ሉቃ.1፥15። እግዚአብሔር የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ከወሰናቸው፥ ከጠራቸው፥ ካጸደቃቸውና ካከበራቸው መካከል ታላቁ ዮሐንስ መጥምቅ መለኮት ነው። ሮሜ.8፥29። ጌታም በወንጌል፥ «ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ የለም» ማለቱ ለዚሁ ነው። ማቴ.11፥11።

ዮሐንስ በድንቁርና ጨለማ ያሉትን ወደ ዕውቀት ብርሃን ክርስቶስ እንዲመራ፥ በኃጢአት ያሉትን በንስሐ ወደ ጽድቅ እንዲመልስ፥ በአምልኮተ ጣዖት የተጠመዱትን ፈትቶ ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር እንዲያመጣ የተመረጠ ነውና «ከእሥራኤል ልጆች ብዙዎችን ወደ ጌታ አምላካቸው ይመልሳል» ተባለ። እሥራኤል አብዛኞቹ በኃጢአትና በበደል ምክንያት ከጌታ ተለይተው ነበርና ነው። በደል ከእግዚአብሔር ይለያል ኃጢአትም ከእግዚአብሔር ቸርነት ያርቃል። ይህም ምሕረቱ፥ ቸርነቱ፥ በረከቱ፥ ረድኤቱ፥ ርኅራኄውና ይቅር ባይነቱ ይሰወራል፥ ይርቃል ማለት ነው። ኢሳ.59፥2።

በነቢዩ በኢሳይያስ እንደተነገረ ቃለ ዓዋዲ ዮሐንስ ለጽድቅ ምድረ በዳ እና በረሃ የሆነውን የሰው ልቡና ጠርጐ አስተካክሉ ምቹ ጐዳና ፍኖተ እግዚአብሔር እንዲሆን የሚያመቻች፥ በኃጢአት ተሸርሽሮ ሸለቆ፥ በትዕቢት አብጦ ተራራ፥ በክፋት ጸንቶ ጠማማ የሆነውን ልብ የተስተካከለ ትሁትና ቀና አድርጐ መሢሕ ክርስቶስን እንዲቀበል የሚያሰናዳ፥ ነቢዩ ሚልክያስም እንደተናገረ በድንገት ወደ መቅደሱ ለሚመጣ ጌታ መንገድን በፊቱ የሚያስተካክል በመሆኑ የተዘጋጁትን ሕዝብ ለጌታ እንደሚያሰናዳ ተነገረለት። መንገድ ጠራጊ መባሉም ለዚህ ነው። ኢሳ. 40፥3። ሚል.3፥1። ሉቃ፥1፥17።

ጌታ በወንጌል ወደ መንግሥተ ሰማያት እንድትገቡ ታላቅም እንድትሆኑ ተመለሱ እንደ ሕፃናትም ሆናችሁ ራሳችሁን አዋርዱ ባለው መንገድ ዮሐንስ መንግሥተ ሰማያት ወንጌል ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ብሎ የሚሰብክ፥ ብዙዎች በትህትና ተዋርደው ለክፉት ነገር ሕፃናት እንዲሆኑ የሚመክር፥ እግዚአብሔርን የመፍራት ጥበብ የጐደላቸውን መንግሥቱንና ጽድቁን ወደ መፈለግ ጥበብ የሚመልስ፥ ከኃጢአት አዋቂነት ወደአለማወቅ ሕፃንነት የሚለውጥ በመሆኑ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልሳል ተባለ። የጻድቃን ጥበባቸው መሠረቱ እግዚአብሔርን ማፍራት ነው። ምሳ.1፥7። ማቴ3፥1። ማቴ.18፥3። 2ቆሮ.11፥20። ፍርሃት ሲባልም መጋቢነቱን፥ ፈጣሪነቱን፥ ጌትነቱን፥ ኃያልነቱን ፀውቆ በመንግሥቱ ሽረት በባህርዩ ሞት የሌለበት ጻድቅ ፈራጅ መሆኑን ማመን ነው።

ሣራ፥ «ካረጀሁ በኋላ በውኑ ፍትወት ይሆንልኛልን? ጌታዬም ፈጽሞ ሸምግሎአል» እንዳለች ዘካርያስም እኔ ሽማግሌ ነኝ፥ ሚስቴም በዕድሜዋ አርጅታለችና ይህን በምን አውቃለሁ? በማለቱ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ይህ ቃሌ እስኪፈጸም ድረስ ዲዳ ትሆናለህ አለው። ሆኖም ዘካርያስ ተገሠጸ። «አባት የሚወደውን ልጅ እንደሚገሥጽ እግዚአብሔርም የወደደውን ይገሥጻልና።» ዘፍጥ.18፥12። ምሳ.3፥11። ሉቃ.1፥18። ተግሣጹ በዘካርያስ ልብ የተከሰተው ጥርጥር እንዲወገድ ነው። ሕዝቡ ለከበረ አባታችን ራእይ ተገልጦለት ነው አሉ እንጂ እንደ ደካሞቹ በኃጢአቱ ምክንያት ይሆን? ብለው አልተጠራጠሩም። ለመፍረድም አልቻሉም። እርሱም የአገልግሎቱ ወራት እስኪፈጸም ድረስ ከቤተ መቅደስ አልተለየም።

እንግዲህ ከዚህ የምንማረው ምንድነው? እኛስ ጸሎታችን እንዲሰማልን ምን እናድርግ? ከሐዘን ይልቅ ደስታን፥ ከጦርነት ይልቅ ሰላምን፥ ከመርዶ ይልቅ የምሥራችን የምንሰማው ምን ስንሆን ነው? ከሥር ጀምሮ ታሪኩን እንደተመለከትነው የሚያስፈልገው ነገር ዘካርያስንና ኤልሳቤጥን ሆኖ መገኘት ነው። ይኸውም በጌታ ሕግጋትና ትእዛዛት መኖር፥ ከጌታ ቤተመቅደስ አለመለየት፥ ከዕጣኑ መሥዋዕት አለመራቅ ነው። ዕጣኑ የዘላለም መሥዋዕት ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና ከቅዱስ ቁርባን አለመለየትን ያመለክታል። ዘካርያስ በቤተመቅደስ

ቢዘገይም ሕዝቡ በትዕግሥት እንደ ጠበቁት ቅዳሴው ቢረዝምም ካህናቱ ከመቅደስ ወጥተው እስኪያቆርቡን በትዕግሥት መጠባበቅ አለብን። እነዘካርያስ ተስፋ ሳይቆርጡ እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ የሚፈልጉትን ለማግኘት እስኪያረጁ ድረስ እንደጸለዩ እኛም እስከመጨረሻው ተስፋ ሳንቆርጥ እንጸልይ። ስንጸልይም በአጭሩ አራት ነገሮችን እናስተውል።

1. መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ.21፥22 «አምናችሁም በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ» ባለው መሠረት ያደርግልኝ ይሆን? ወይስ አያደርግልኝ ይሆን? እያልን ሳንጠራጠር በእምነት እንጸልይ። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ «ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጐድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን። ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን። የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕር ማዕበል ይመስላልና። ሁለት አሳብ ላለው በመንገዱም ሁሉ ለሚወላውል ለዚያ ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች የሚያገኝ አይምሰለው» በማለት አስተምሮናል። ያዕ.1፥5። የጥርጥር ማዕበል በልባችን ውስጥ የተነሣ እንደሆነ ኑሮአችን ሁሉ ማለት ሥጋዊውም ሆነ መንፈሳዊው በሁከት የተሞላ ይሆናል። የምንሻውንም አናገኝም። ይህ እንዳይሆን ነው የእምነት ጸሎት የሚያስፈልገው። እንዲያውም እግዚአብሔር የነገሩትን የማይረሳ የለመኑትን የማይነሳ አምላክ ነውና «የጸለያችሁትንና የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ ይሆንላችሁማል» ትዕግሥቱ ካለ መቼም ይሁን መች አያስቀርባችሁም ማለት ነው። ማር.11፥23።

2. የምንለምነውን እንወቅ። የዘብዴዎስ ልጆች እናት ሳታውቀው ለልጆቿ መከራና ሞት እንደለመነች ጌታም «የምትለምኑትን አታውቁም» እንዳላት እኛም አለማመኑን አጥተንበት ጌታ ጨክነብኝ ሰንል እንዳንገኝ ምን እንደምንለምንና ለምን እንደ ምንለምን ማወቅ አለብን። የሚቀረውን ርስት ምድራዊ ሳይሆን ርስት ዘላለማዊ መንግሥቱን፥ የሚጠፋ ሀብትን ሳይሆን የማይጠፋ ሀብትን መንፈስ ቅዱስን፥ ሥጋዊ መብልን መጠጥን ሳይሆን መንፈሳዊውን ሥጋ ወደሙን እንለምን ይሰጠናል። «ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፤ ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል» ተብለናልና። ማቴ.6፥33። መንግሥቱን ሲል ሃይማኖትን ጽድቁን ሲል ምግባርን ነው።

«የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ ከመጐምጀትም ሁሉ ተጠበቁ» መባሉ ለዚህ ነው። ሉቃ.12፥13።

3. እንደ ፈቃዱ እንጸልይ። ሐዋርያው ዮሐንስ፥ «በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው። እንደፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል የምንለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመንነውን ልመና እንተቀበልን እናውቃለን» ባለው መሠረት የእርሱ ፈቃድ መንፈሳዊውን ነገር እንድንለምነው ነው። 1ዮሐ.5፥14። የሚቄን ሞት አይፈቅድምና ከዘላለም ሞት አድነን ብለን እንለምነው። ሕዝ.18፥32። ለዚህም ከኃጢአት መመለስ በደልን ማራቅ ተገቢ ነው።

4. በጸሎታችን ኃጢአታችንን እንናዘዝ «ቂም ይዞ ጸሎት ሳል ይዞ ስርቆት» አይሆንምና አስቀድመን በሕይወታችን ውስጥ ያቈምነውን ኃጢአት በንስሐ ማስወገድ ይገባናል። በተቋረጠ መስመር ስልክ መደወልና በኃጢአት ሆኖ መጸለይ አንድ ነው። ነቢዩ ኢሳይያስ፥ «የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም። ጆሮውም ከመስማት አልደነቆረችም። ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች። እንዳይሰማም ኃጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል» ብሎናል። ኢሳ.59፥1። ስለዚህ ራስህን ለካህን አሳይ ባለው መንገድ ኃጢአታችንን ተናዝዘን በንስሐ ታጥበንና ነጽተን እንጸልይ። አበው «ልብስ ሲያድፍ በውሃ፥ ሰውነት ሲያድፍ በንስሐ ይነጻል» ይላሉ።

ያን ጊዜ በምድር የታሰረው በሰማይ የተፈታ ይሆናል። ካህናቱ ይቅር ሲሉን በእርሱ ዘንድም ይቅር እንባላለን። ማቴ.8፥4። ማቴ.16፥19። ማቴ.18፥18። ዮሐ.20፥23። ከሁሉም አስቀድመን ግን የሰማዩ አባታችን ይቅር ይለን ዘንድ የበደሉንን ሁሉ ከልብ ይቅር ማለት አለብን። ማር.11፥26። «ሲበድሉ ማሩኝታ ሲበደሉ ይቅረታ የክርስቲያንነት ምልክት ነውና።»

መቼም ሁላችንም በዚህ የምንመራ ከሆነ ጸሎታችን ተሰምቶ ከማኅጸን የተባረከ ልጅ ከሜዳ የተባረከ ፍሬ እናገኛለን። የሰማዩ አባታችን እንኳን ለምነነው ሳንለም ነው የሚያስፈልገንን የሚያውቅ ነው። ማቴ.6፥8 በኤርምያስ አድሮ፥ «ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ ዐውቃለሁ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም። እናንተም ትጠሩኛላችሁ። ሄዳችሁም ወደ እኔ ትጸልያላችሁ። እኔም እሰማችኋለሁ። እናንተ ትሹኛላችሁ በፍጹም ልባችሁ ከሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ ከእናንተም

ዘንድ እገኛለሁ» ያለ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ተናዝዘን የምንለምነውን አውቀን እንደ ፈቃዱ በእምነት የምንጸልየውን ጸሎት ይሰማናል። ዘወትርም በበረከቱ በረድኤቱና በቸርነቱ ከመካከላችን አይለይም። ኤር. 29፤11።

አበው «የሺ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ» እንዲሉ የጽድቅ ሁሉ ማሰሪያው ቅዱስ ስጋውና ክቡር ደሙ ስለሆነ የዘለዓለም ሕይወትን ለማግኘትና ከእርሱ ጋር አንድነትን እንዲኖረን ዘካርያስ የአገልግሎቱ ወራት እስኪፈጸም ድረስ ከመሰዊያውና ከዕጣኑ መስዋዕት እንዳልተለየ እኛም የተፈቀደልን የአገልግሎት ዕድሜ በሞት እስኪፈጸም ከመሰዊያው ታቦትና ከዘለዓለሙ መስዋዕት ከኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም አንለይ፤ ዮሐ. 6፤54። ዘካርያስ ሁሉን ፈጽሞ ወደ ቤቱ እንደሄደ እኛም ዘመናችንን ፈጽመን የማይቀረውን ወደ መቃብር ቤት መግባት አለብን።

ልዑል እግዚአብሔር በቸርነቱ ጸሎታችንን ተሰሚ፤ መስዋዕታችንን ጉዳይ ፈጻሚ ያድርግልን።

ዲያቆን ተክለ ወልድ
ሐመር የካቲት 1985 ዓ.ም